# ኢህአፓ « አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም!! »

► ይህአባ (ኢህአፓ) እውነት አረጀ??? ለሚለው በደብተራው ዌብሳይት
የትርሲትና የድላይ መጣጥፍ የተሰጠ ምላሽ

*እንዳለው ምትኩ*

የኢትዮጵያ ህዝቦች ለዘመናት ሲፈራረቁባቸው በነበሩ ግፈኛ መሪዎችና አስተዳደሮች የተነሳ ያሳለፉት የሰቆቃ ግዜአት የታሪካችን ጥላሸት ከመሆን የሚድን አይመስለኝም:: ይህ ግፍና ሰቆቃ ደግሞ ከህዝብ አብራክ የተፈጠሩ ወጣቶችንና ሀገር ወዳድ ወገኖችን ለትግል በማነሳሳት የግፈኞች ስርዓት እንዲያከትም የደም ግብር ሲከፈል ቆይቷል:: በአፄ ኃይለስላሴ ስልጣን ዘመን ተማሪውና ምሁሩ ህዘባዊ የሆኑ ጥያቄዎችን በማንሳት የንጉሱን ዘመን ህዝባዊና መለኮታዊ መሰረት እንዲሸረሸር በማድረግ ስርዓቱ መግዛት ከማይችልበት ደረጃ ደርሶ እንዲኮታኮት ሰፊና ጉልህ ሚና ተጫውተዋል::

ንጉሱ እንደቀድሞው መግዛት ሳይችሉ ቀርተው ስልጣናቸውን ቢለቁም የህዝቡን ትግል አስተባብሮ ለመምራት የሚችል የተደራጀ ስብስብ ባለመኖሩ ወታደሩ ያለ ሁነኛ ተቀናቃኝ ስልጣን ላይ መውጣት ቻለ:: ስልጣኑ እየጣመው በሄደ ቁጥርም ከቀደምት አባቶቹ በከፋ መልክ የግፍን፣ የሰቆቃን፣ የግድያ፣የዝርፊያ፣ የማሰቃየት፣ ወ.ዘ.ተን ልጓሙን በማጥበቅ ስልጣኑን ይበልጥ ለማጠናከር ጣረ::

ይህ የግፍና የሰቆቃ አገዛዝ ሲጀምር የተፈጠረው ኢህአፓ ባነሳቸው ህዝባዊ አላማዎችና ለዘመናት በአታጋይ ድርጅት እጦት ሲያንገበግበው የነበረ ህዝብ፣ በሙሉ ልቡ አምኖ ተቀበለው:: በ60ዎቹ መጨረሻና በ70 መግቢያ አካባቢ ኢህአፓ ያልሆነ ኢትዮጵያዊ ፍጡር ማግኘት አዳጋች እስኪሆን ድረስ በህዝቡ ጉያ ውስጥ መግባት ቻለ:: ያለፉት ዘመናት አገዛዞች ግፍ ያስመረረው ህዝብ ሌላው ቀርቶ በቁስ አካላዊነት ላይ የተመሰረተው የዕምነትና የሀማኖት መሸርሸር ኢህአፓን ጉግ ማጉግ ብሎ እንዲያወግዘው አላደረገም:: ብቻ ትንሽ ከትልቅ ሳለይ፣ ሙሁር ከማሀይም ሳይመርጥ፣ ወታደሩን ከሰቪል ሳያዳላ፣ለአንድ ዓላማ አሰለፈው::ያውም «ለጊዜአዊ ህዝባዊ መንግስት::» እየዋለ እየአደረ ግን የትግሉ መልክ ቅጥ እየአጣና በከተማ ብቻ እየታጠረ ፣ኢህአፓ አንድ በገደለ ቁጥር ከሱ ሺ እሞተበት በመነጠራወዝ ትግሉን ሊመራ ቢሞክርም፣ በብቁ ታክቲክም ሆነ

ስትራተጂ የተደገፈ አልነበረምና ጠብ የሚል ነገር ጠፍቶ ጭረሽ በከተሞች ትግሉ እየነጠፈ፣ ለመደበቂያ በተዘጋጁ የገጠር አካባቢዎች መወሰን ተገደደ።

በዕምነትና በመርህ ሳይሆን በአማራጭ እጦት የተጀመረው የገጠር ትጥቅ ትግል ከአርሶአደሩ ጋር በአካልና በዕምነት የተቆራኘ ስለአልነበር፣ ውጊያው ከጠላት ጋር ከመሆን ይልቅ ከገበሬው ጋር መሆን ገባ። ይህንም ድርጊት በአርማጭሆ፣ በደንገል(ጭልጋ) ፣በሰራቆ፣ በዳዋና አዳኘ አገር በመሳሰሉ የምዕራብ ጎንደር አካባቢዎች የተደረጉ የአርሶ አደር ግጭቶችን ዕማኝ መጥራት ብቻ ይበቃል። ጭራሹን ከ73 ዓ.ም(እ.ኢ.አ) በኃላ በቋራ የነበረው ኢህአፓ ትጥቅ ትግል በሃይል ይካሄዳል የሚል ዕምነት በመያዝ አርሶ አደሩ በመቸውም ጊዜ ሊረሳው የማይችል የአካልና የገንዘብ ቅጣት ይጥልበት ያዘ።

ኢህአፓ መሰረታዊ ዓላማው የተዛባና በዚህ ጉዞው ማንንም ነፃ ማውጣት እንደማይችል የተረዱ ወገኖች ገና በጊዜ ከድርጅቱ በመሰናበት የስደት ኑሯቸውን ማማሟቅ ጀመሩ። ስህተቴን ገመገምኩ በማለት «በግምገማ ዕርማት በግለ ሂስ ዕድሳት» በማለት ሽንቁሩን ሊደፍን ሲጀምር በቋፍ ላይ እንዲሁም በውስጣዊ ጥርጥር ላይ የነበረው አብዛኛው የበታች ታጋይ ጭራሽ ትግል አያሳየኝ ብሎ ግማሹ በምህረት ወደ ጠላው መንግስት ሲገባ፣ ግማሹ ደግሞ ለስደት ተዳረገ። ለዚህ ነው በ1979 (እኢአ) ብዕረኛው «ተከዜ» በሚለው ግጥሙ ይህን የተቀኘው፡-

« .........ችግኞችና ዛፎች ቆራርጠህ ያስከተልካቸው
ፀደይ አብቅቴ ሲነጋጋ በጋው ላይ ወዴት ጣልካቸው?
አይ ተከዜ የክረምቱ ጉረኛ ዱያል መሳይ አጭበርባሪ
ማደሪያውን ሳከዋውን አለት ጭንጫ ይዞ ዟሪ
በመከራ ኩሬ ሰዳጅ አንጀት ባንጀት አስቆጣሪ
ደመና ሲቀር አሉሁ ባይ ጀንበር ስትሰርቅ በራሪ
መጥፎ ተከዜ ነገረ ሰሪ።
ትንሳኤ ሞት የሌለው ሞት ገለህ ወርውረህ ስትጥለው
መኖሩን ሳይኖር እንዲኖር በመከራ ሳንቃ ስትመግበው
ወዙ ለህዩ ችፍ እንዳለ የግፍ አዝመራ ስትመግበው
ወደ ምድረ ፍዳ ስትማግደው
ተከዜ ያንተን ስጋ ይህስ አልኩህ ይህስ ግፍ ነው።

አልፋ ኦሜጋ ፀፀት ነው፡፡
የወሎ የበጌምድርን የትግራይን የፀለምትን
የዳሩን ሳይቀር የመሀሉን የከተማ የገጠሩን
ለጋ ለምለሙን አግበስብሰህ በጊዜ ወኔ ትዕቢት ሞልተህ
ስር የሰደደ ዋርካ ሳይቀር ፈንቅለህ ፈንግለህ ጥለህ
ቋጥኝ ከጠጠር አጋጭተህ
መካሄጃህን ሳታጣራ ስንቱን አሸዋ ቀበርካቸው
ስንቱን ቸረቸርካቸው
ስንቱን አጠፋሃቸው
ስንቱን ካገር አውጥተህ ሱዳን በርሀ ዘራሀቸው፡፡» በማለት በምሬት ሀቁን የፃፈው፡፡

ስለዚህም ኢህአፓ በአገራችን የነበረውን እንቡጥ ለጋ የዴሞክራሲ ትግል በትክክለኛ መንገድ ሊመራው ባለመቻሉ ብዙ ቆራጥ፣ ደፋር፣ በፈጠራና ክህሎት የተሞሉ ወገኖቻችን እንድናጣ ተደረገ፡፡ይህም ያመራር ጉድለት ከሞት የተረፈውን ታጋይ ትግል አያሳየን ብሎ በየምርጫው ለዕለት ጉርሱ ብቻ እንዲጣጣር አደረገው፡፡ የተወሰነውም ርስ- በርሱ ሲገናኝ ያለፈበትን የትግል አካሄድ ለትዝታና ለወግ ማጣፈጫ ከመጠቀም በላይ ራሱን ገለልተኛ አድርጎ ማለፍን መረጠ፡፡

ከዚሁም ጋር በተለያየ ደረጃ አመራሩ ውስጥ የነበረ ተስፋ ያልቆረጠ ጢቂት አካል ያለፈውን የጀግኖች ሞት እሱን ለማቆየት የተደረገ ይመስል ያን እየአነሳ የረጅም እድሜ ባለፀጋ ነኝ ይለናል፡፡ በራሱ የአመራር ጥፋት ያጣናቸው ወገኖቻችን የውስጥ እሳት ሆኖ እየአንገበገበን ባለበት ገዜ ዓይኑን በጨው የታጠበው የኢህአፓ ትርፍራፊ አመራር ሌላ ዕልቂት ለማምጣት በየተደበቀበት ጓዳ የጥፋት አታሞውን ከመምታት አልተቆጠበም፡፡ «በእርጅና ዘመኔ ለኔ የሚሞቱ በዝተዋል» ይለናል፡፡ በነትርሲት መጥጥፍም ለመዝፈን የተፈለገው ዘፈን ይሄው ነው፡፡

ትግሉን በግንባር ቀደምትነት ሲጋፈጡ የነበሩና ከሞት የተረፉ ታጋዮች፣ የኢህአፓ አመራር በትምክህትና በዕብሪት የተወጠረ የወቅቱንና ተጨባጭ የትግል

ስልቶችን መንደፍ የተሳነው፣ ከህዝብ የተለየ መሆኑን አጋልጠው ድርጅቱን ቀብረው ተለያይተዋል፡፡ከዛ በኃላ በውጭ አገር ውስጥ ከየተደበቀበት ምቹ ጊዜ ያገኘ ሲመስለው ብቅ የሚል አመራር ለህዝባዊ ዓላማና ተልዕኮ ራሳቸውን በቆራጥነት ወስዋዕት ያደረጉ ታጋያ ሰማእታትን ሊወክል አይችልም፡፡እነሱም በአካል ቢኖሩ  ይህን ግፈኛና ፀረ-ዴሞክራሲ አመራር ለጥፋተኝነቱ እነዲጠየቅ ከማድረግ ወደ ኃላ የሚሉ አይሆኑም፡፡ ህያው የዴሞክራሲና የነፃነት አላማቸው ይህንኑ ተግባር በሚፈፅሙ ወገኖቻቸው ዕውን ይሆናል እንጂ፣ ምኞቱን ባመከኑ ፣ትግሉን ባዶለደሙና ባኮላሹ ወገኖች አይረጋገጥም፡፡

የእነዚህ የአገራችን ኩራት የሆኑ ቆራጥ ታጋይ ሰማዕታት ዋና አላማ የተጎሳቆለው የኢትዮጵያ ህዝብ ኑሮ እንዲሻሻል፣ የህዝቡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲአዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሁሉም ህዝቦች ማንነት ጥያቄ እንዲከበር ነው፡፡ታድያ ለዚህ አላማ ምንም ይሁን ምን የሚታገሉና ተግባራዊ የሚያደርጉ የሰማዕታቱን ውጥን ግብ ለማሳካት የሚጥሩ ናቸው፡፡

በተቃራኒው የህዝቡን የልማት እንቅስቃሴ ለመቀልበስ፣ የዲሞክራሲ ጅምሮችን ለማጣጣል፣ የህዝቦችን እኩልነት ለማነወርና ለማቃለል የሚጥሩ ደግሞ  ታጋይ ሰማዕቱ ቁመውለት የነበረውን አላማ የሚፃረሩ ተግባራዊ ጠላቶቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም አሁን በየጓዳውና ታዛው ምቹ ጊዜ ጠብቆ አለሁ የሚለው ትርፍራፊ የኢህአፓ አመራር ጀግኖች ሰማዕታትን አይወክልም፡፡ የእውነተኛውን የኢህአፓ ትግልና ዓላማ እንደገደለ ሁሉ በአገራችን ጭል ጭል የሚሉ ጀምር መልካም ስራዎችን ለማጥፋት የሚሯሯጥ ወሬ ለቃሚና አልባሌተኛ ነው፡፡ ይልቅ ይህ አመራር ትግሉን  ማኮላሸቱን አምኖ ንስሀ ቢገባና አልሞትኩም ብየ አልዋሽም  ቢል ለወደፊት ትግል  አዲሱ ትውልድ ትምህርት ሊወስድበት ይችላል፡፡

ስለዚህም እነትርሲት ኢህአፓ አይደለም ማረጀት ቀደም ብሎ የሞተ ድርጅት ነው፡፡ ይህንም ሞቱን ያፋጠኑት በተለያየ ደረጃ የነበሩና ያሉ አመራሮቹ ናቸው፡፡ኢህአፓ የሞተው ሀቀኛ አላማው ተዛብቶ ለስልጣን ጥመኞች ግብ ማሳኪያ የሆነ ዕለት ነው፡፡ አህአፓ የሞተው አምባገነን መሪዎች ድብቅ

አላማቸውን ለማሳካት የተንቀሳቀሱ ጊዜ ነው::ኢህአፓ የሞተው የህዝብን ጥያቄ ባግባቡ መመለስ ተስኖት በህዝብ ተተፍቶ በሃይል ከያዛቸው ቦታዎች ሲባርረ ነው::ኢህአፓ የሞተው  በብዙ ሺ የሚገመት የድርጅቱ አባልና የበታች ታጋይ በአመራሩ ዕምነት አጥቶ ወደ ተለያየ ቦታ የተበታተነ ጊዜ ነው:: ለዚህም ገጣሚው «በተከዜ» ግጥሙ የሚከተለውን የገለፀው:-

« ድንገት ደርሰህ ድንገት ጠፊ
አድራሻ የለህ ተወንጫፊ
የክልስ አባይ አነፍናፊ
ጨቆቀትህን ሳታፀዳ ብዙ ጅረቶችን አቃፊ::»

ዛሬ በረጂም እድሜ ስም ሊመፃደቁ የሚቃጣቸው ትርፍራፊ የኢህአፓ አመራር፣ ትርጉም ያለው ትግል ስልት መቀየስ ተስኗቸው፣ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ መኖራቸውን ለማሳየት አገታቸውን ቀና ለማድረግ ይጣጣራሉ:: ሰሚ ሳይኖራቸው ያላችው ስለሚመስላችው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ሊሰባሰብ በሚሞከርባቸው አካባቢዎች በመገኘት ስውር ተልኳ ቸውን ለማሳካት ይጥራሉ::በየሰበካ ጉባኤው በመጋባት አትዮጵያውያኑን በተራ መለያየት ላይ እንዲነታረክ መንገዱን ይጠርጋሉ:: ከዚህ ሁሉ በላይ እንዲያው ባጋጣሚ መንግስት ቢወገድ ለስልጣን እንበቃለን ብለው ያስባሉ::

ከዚህ ሁሉ ጋር ግን አንድ የማያሰቡት ነገር እንደ ጥላ ከኃላቸው የሚከተላቸው መሆኑን አይገነዘቡም:: በተሳሳተ የትግል ስልት በከተማና በገጠር ያስፈጁት ህዝብ፣ ልዩነትን ያነሳል ብለው ራሳቸው የፈጁት ታጋይ ደም ተጠያቂ ከመሆን እንደማይድኑ ነው:: ጊዜው ደርሶ ይህ እስኪሆን ሞት ካልቀደማቸው የዕድሜ ባለፀጋ ነን ከማለት የሚከለክላቸው  የለም:: እኔም ለአባባሌ መቋጫ ከተከዜ የግጥም ስንኞች ጥቂቱን ልዋስ፣

«የሰላም ጅረት አደፍራሽ
ተከዜ ጉግ ማንጉግ ደራሽ
እስከ አሁን ፣አይቸህአለሁ ፣አይቸህአለሁ ታዝቤህአለሁ
አየሁ ባይም ትዕግስት የለኝ ዛሬስ አጋልጥአለሁ

የወጣት ሙሁራን መቅሰፍት ፀረ እድገት ብየህአለሁ፡፡
ታድያ ገና. . .
ሲቃ ሰቆቃ እሸሩሩ
ላለፈ ክርምት ቤት አይሰሩ
ባለፈው ላላጋህቸው
ላጋጨህ ለገደልካቸው
ትቢያ ውስጥ ለቀበርካቸው
ዱር በርህ ለጣልካቸው
እንዲ እንዲያ ላረግህቸው
ታሪክ ላይምርህ ተማፅነዋል ተከዜ የርግማን እጣ
አንተን ቀጥተን ልንበቀል በደላችንን ልንወጣ፡፡»